## ይድረስ ለየሃባ (ኢህአፓ) ታጋይ አያልነሽ፡ ያልሰማሽውን ጉድ ልንገርሽማ

ባለሽበት ሰላምታዬ ይድረስሽ እላለሁኝ።

ወፍ ያላወጣቸው ደፋ ብለው ሲቀሩ፤ ወፍ ያወጣቸው ደግሞ ተሰደው ውጭ ዳያሰፖራ ከሚሉት አገር መጥተው ይኖራሉ። ያው ያኗኗሩ ሁኔታ የተለያዬ ነው። ግማሹ ሰርቶ እንኳን ለራሱ ለሌላ ሰው ተርፏል። ግማሹ ቢሳካለትም ባይሳካለትም ደስ አላለውም። የድሮውን እያስታወሰ ምነው ከዚህ አገር ባልመጣሁ እያለ ሲተክዝ ይውላል።

ሰሞኑን ስለ ዲያስፖራ የሃባ (ኢህአፓ) የተወራውን ሰምተሽ ይሆን? ወደ 81 ሺህ ያማሪካ ዶላር የሃባ ላማሪካ አፈ-ቀላጤ ከፈለ ሲባል ሰማን። መጀመሪያ ማመን አቃተኝ። ለማረጋገጥ ካማሪካው ፍርድ ሚኒሰትር ዲህረ-ገጽ ላይ የየሃባን ዶሴ አግኝቸ ስመለከት፤ በጀረንጆች አቆጣጠር በ2004 አ.ም. የሃባ 27 ሽህ ዶላር ለአፈ-ቀላጤ ከፍሏል የሚል መረጃ አለ። ጠለቅ ብዬ ብፈልግ የቀረውንም አረጋግጥ ነበር። ግን 81 ሽህ ሆነ 27 ሽህ ዶላር፤ ነገሩ ይህ አይደለም። ዋናው ጥያቄው ለምን ገንዘቡ ለአፈ-ቀላጤ ተሰጠ ነው። ያገኘሁት መረጃ እንደሚያመለክተው፤ አፈ-ቁላጤው ካማሪካ ባለስልጣኖች ጋር ተገናኝቶ ትንሽ ምኒምኒ ምኒምኒ ብሎ ተናግሮ እና የሆነ ወረቀት ሰጥቶ እንደሄደ ነው። ለዚች ስራ 27 ሽህ ዶላር!

ለምን አፈ-ቀላጤ አስፈለገ? የምትይ ከሆነ ነገሩን ላስረዳሽ። ያ አፈ-ቀላጤ ያማሪካ ባለስልጣኖችን እንዲያነጋግር፤ የሃደግ (ኢህአድግ) የጦቢያን ህዝብ እየጨቆነ ነው፤ እና የሃደጉ መሪ መለስ ዜናዊን እንዲቆጡት፤ እምቢኝ አልሰማችሁም ካለ ደግሞ ለጦቢያ መንግስት አማሪካ የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ ርዳታ አትስጥ፤ መለስ ዜናዊ የግድ ርዳታው ሲቀርበት እሽ ይላል ተብሎ ታስቦ ነው። ያላወቁት ነገር፤ መለስ ድርቅናም ትግሬ፤ ከተቆጣ እንኳን ያማሪካን ፈረንጅ ቀርቶ የገዛ ሚስቱን፤ ብትር ይዛ የምትነሳውን ሀይለኛ ወልቃይቴ፤ አያዳምጣትም፤ የተረገመ (ሀይለኛ) አይደል! ታዲያ ዙሮ ዙሮ ርዳታው እንዲቋረጥ ነው።፡ምን ጊዜም የኛን ዘመዶች ፤ የሃባን ካድሬና ጦር ሲቀልቡ የነበሩት፤ ቢራቡ ቢጠሙ ያለኛ የሚያስብላቸው የለም።

አይ አያልነሽ፤ ስንት ስንት ያልሰማሺው ጉድ አለ። የራሷ ሲያርባት የሰው ታማስላለች እንዲሉ፤ እዚህ ያሉ የሃባዎች የራሳቸውን የድርጅት ስራ ትተው፤ በሰው ጉዳይ እየገቡ፤ ስለ ሰው እየተረኩ፤ ካንዱ ጋር ህብረት፤ ከሌላው ጋር ግንባር እያሉ፤ እንዴት ያለውን ድርጅት ተለጣፊ ድርጅት አድርው፤ ዛሬ የሃባ ማለት ቁም ነገር የሌለው ወረኛ ማለት ሆነ። ስለሰው ጉዳይ እንጂ ስለ ራሳቸው ጉዳይ አይናገሩም።፡ በያመቱ ያው ያ መከረኛ እግር ኳስ ጨዋታ አለ፤ ምድረ-የሃባ የተባለ ከዚያ ነው የምታገኚው። ግማሹ ውጫጩን እየጎተተ፤ ግማሹ አርጅቶ ጎብጦ፤ ግማሹ ደግሞ እንደፎገላ (እንደጎረመሰ) ታገኝዋለሽ። ያው ያቺ መከራኛ ስብሰባ ትጠራና አንዱ የሃባ ረዥም ንግግር ያደርጋል። ስለ ተጨባጩ ሁኔታ፡ ያው እንደተለመደው ሌሎች የሚሰሩትን መተንተንና ማውገዝ ነው። ከዚያ ቀጥሎ መብሉ፤ መጠጡ፤ ሳቅና ጨዋታው አለ፤ ባጠቃላይ የደስታ ጊዜ ይሆናል። ታዲያ ይህን እያዩ የሃባ መሪዎች ጠገቡ (ባለጉ)። በየሃዱበት እንደ ንስሃ አባት ፉፉፉፉ ይባላሉ (ይስተናገዳሉ)፤ ማንም እኛን የሚጠይቀን የለም ብለው ደምድመው ቁጭ! ያ አልበቃ ብሎ ደሞ ርስ በርሳቸው  ተጣሉ።  አይ አያልነሽ፤ ጠግበው። እንዳንቺን የጸሃይ ሀሩርና የሌሊት ብርድ ይነካቸዋል? የጠገበ በሬ መሬቱን በቀንዱ ሲቆፍር ይውል የለም። ገበሬው ሲያርሰው የዋለ ቀን እማ እንኳን መሬት በቀንዱ ሊቆፍር ቀርቶ ሳር የሚግጥበት ጊዜ የለውም። የሃባ መሪዎችም በሌላ ድርጅት ገብተው ነገር የሚፈተፍቱትና የሚጣሉት የሚሰሩት ስራ ለሌላቸው ነው። ስሩ ብሎ የሚናገራቸው ጠፋ። ከዚህ ወዲያ የሃባ የተባለ ሁሉም ሰው ተሰብስቦ ድርጅቱን ወይንም ተገድሎ እንዲቀበር ወይንም ተደግፎ ወደፊት እንዲራመድ መወሰን ያስፈልጋል፡ እየተባለ ይነገራል እልሻለሁኝ።

እንዲያው ለመሆኑ እኔንማ እኮ የዳያስፖራው ቦለቲካም ከጅሎኝ (ጀማምሮኝ) ነበር። ወዲያው የሃደግ እንደገባ (ስልጣን እንደያዘ) እና ወልቃይት ወረዳ ወደ ትግራይ ክልል የሄደ ሰሞን ተቆጥተን ነበር። ታዲያ ቶሮንቶ ካናዳ የሚኖረው አንዱ ጎንደሬ፤ እኒህ ወያኔዎች መጀመሪያ እህቶቻችን (ወልቃይቴዎችን) ሙልጭ አድርገው አገቧቸው፤ ያ አልበቃ ብሎ ደግሞ መሬታችን ወሰዱ። ጎበዝ እንግዲህ በቃ፡ ጥቃት ገባ አለና ስብሰባ ጠራ። እኔም ጥሪውን ተቀብዬ ወደ ስብሰባው እዬገሰገስኩ ሄድኩኝ። ከቤቱ ጓሮ ተሰበሰብነ። ከፋኝ ስለሚባል ተዋጊ ድርጅት በሰፊው ገለጣ ተደረገ። መዐት

ፉከራ ወረደ። ትንሽ ቆይቶ ምግብ መጣ። እንጀራውና ቀዝቃዛው ቢራ ናፍቆኝ ስለሰነበተ ቶሎ ቶሎ ገፋ ገፋ አድርጌ አስገባሁትና ሆዴ ጢን ብሎ ቢሞላ ፈዘዥኩኝ። ሌሎቹ ግን ስብሰባውንና ፉከራውን ቀጠሉበት። የከፋኝ ደጋፊ ኮሚቴ እንዲቋቋም ተወሰነ። እኔም ቦለቲካ እንዲህ ከሆነችማ ጥሩ ነው፤ ቢያንስ ቢያንስ ምግቡንና ቀዝቃዛውን ቢራ ተመልከተው፡ ብዬ በልቤ ተናገሬ ወደ ትምህርቴ ተመለስኩ። በኋላ ስብሰባ ይጠሩኛል ብዬ ብጠብቅ ብጠብቅ ብጠብቅ፤ አምላክሽ አለ አያልነሽ፤ ጠፉብኝ፤ ለካስ አንድ ኢዳቅ (ኢዴሃአቅ) የሚባል የየሃባና የምሶን (መኢሶን) ግንባር ድርጅት ተመስርቶ ወደዚያ ተንጋገተው ሄደው። ኢዳቅ አጠቃላይ ስብሰባ በጠራበት ጊዜማ እኔም ምናባቱ ብቻየን ምን አረጋለሁ አልኩና ወደ ስብሰባው ሄድኩኝ። ያው ገና ስብሰባ ቦታ ብቅ ስትይ የጦቢያን ህዝብ ነጻ ለማውጣት መዋጮ አድርጉ ነው የሚሉ። እኔም ተማሪ ነኝ ብዬ ሳልከፍል ወደ ስብሰባው ገባሁ። በስብሰባው ጊዜ ደግሞ ለሃገራችን መዎጮ አሉ። እኔ ወንድምሽ ያልሰማሁ ያላዬሁ መስዬ ዝም። ሌላው የዋህ ጦቢያዊ እጁን ዘረጋ፤ ኬሻው በገንዘብ ሞላ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ድግስ አለ ተባለና ሄድነ፤ የመግቢያ ይከፈላል ተባልነ፤ እኔም አሁንስ ይበቃል አልኩና ከፍዬ ገባሁ። ያው ከገባሽ በሓላ ደግሞ ምግቡን መጠጡን በሁለት ሶስት እጥፍ ዋጋ ነው የሚሸጡት፤ ላገር ጉዳይ እየተባለ። መቸም አንድ 40 ብር አውጥቸ እራሴን እያከኩ ወደ ቤቴ ሄድኩኝ። ጥያቄው እንግዲህ ያ ሁሉ ገንዘብ የት ሄደ ነው። አይ አያልነሽ፤ ከዚህ ላይ ኩነኔ አንግባ። የሃባዎች ስርቆት አልተማሩም። አይሰርቁም። በፍጡም (በፍጹም)። ውሸት ምን ያረጋል። የነሱ ችግር ምንድነው፤ ነገር መደብቅ። እንኳን ገንዘብ ቀርቶ የሃባ መሪ፤ ምክትል መሪ፤ ጣፊ፤ ምክትል ጣፊ፤ ወዘተ፤ ስማቸው ማን እነድሆን፤ የት እንደሚኖሩ አይታወቅም። ገንዘቡ ግን እንዳልኩሽ ለአፈ-ቀላጤ ተሰጠ። ያው አንድ አፍታ ያማሪካን ባለስልጣኖች ተገናኝቶ ምኒምኒምኒ ምኒምኒምኒ ብሎ ለመውጣት ነው እኮ። 40 በሬን አፈ-ቀላጤ በልቷት ቀረ።

አንቺም እንግዲህ ጫካ መኖሩ ይብቃሽ። ሁኔታው ለውይይትና ለስምምነት አመቺ ነው። ከህዝብ ጋር ተሰልፎ እያደራጁ ማሳተፍ ነው እንጂ በጠመንጃ አፈሙዝ ለውጥ ማምጣት አሁን ቀርቷል። የሃደጎችም ለድሃው ሰው የጤና ጣቢያውን፤ ትምህርት ቤቱን፤ መንገዱን ሌላም ሌላም ጠቃሚ ነገር እየሰሩ ናቸው። ጎንደርና ባሃርዳር አንዳንድ የድሮ የሃባዎች መንግስት ውስጥ እየሰሩ ደካማውን ህዝብ ሊደግፉ ሲሯሯጡ አይቻቸዋለሁ። በየሃደግ የታሰሩትን የሃባዎችንም እንዲፈቱ እየጮሀን ነው። ቢሆንም እነሱ የሃደጎች ይሻላሉ። በቅርብ ጊዜ ውስጥ ስንቱን ድሃ ህዝብ ከሞት አዳኑት። እነዚያ የድሮዎቹማ ሰገብጋባ ሆዳሞች ከራሳቸውና ከዘመዶቻቸው አልፈው ለኢትዮጵያ ህዝብ ምን አደረጉ? ያም ሆኖ ዛሬ ከዚህ ከዳያስፖራ ሆነው ስልጣን መልስን እንይዛለን እያሉ ይታገላሉ። ግን አልሆነላቸውም። ያካባቢአቸው ህዝብም ተንጋግቶ የስብሰባ አዳራሹን ይሞላና ይደነፋል። እነሱም ያን ድንፋታ ተገን ያደርጉና ግራና ቀኝ አያዩ፤ የፖለቲካ መላና ዘዴ አይፈጥሩ፤ ተሰናክለው ይቀራሉ። ጦቢያን እንወክላለን እያሉ እያወሩና እየጣፉ እኛ ጭምር በነሱ የተነሳ የወዳጅ የጠላት መሳቂያ ሆነ።

ክፉም ሆነ በጎ ቢደርስብሽ ግን፤ እንዳንቺ ያለ ጀግና በሁኑ ሰአት ጦቢያ ምድር ውስጥ እንደሌለ እንድታውቂው እንፈልጋለን። ውሸት ምን ያረጋል። ታሪክሽ ይጣፋል። ይሄው በአሁኑ ሰአት ከአጼ ሃይለ ስላሴ ይልቅ በላይ ዘለቀ ወይንም ተስፋዬ ደበሳይ ወይንም ጥላሁን ግዛው ወይንም ወንድማማቾች ገርማሜና መንግስቱ ነዋይ ሲወሱና ሲፈከርላቸው ይውላሉ። ንጉስ ተብዬው ከባናዳዎች ጋር ተንኮልና ነገር ሲጠነስስ ጣልያኖች የሰሩትን መንገድ እንኳ ሳይጠግን፤ አገሪቱን ሙልጭ አድርጎ በልቶ፤ ለወዳጆቹም አብልቶ ለቀቀ። ስሙ በክፍ እንጂ በበጎ የማይወሳ ሰው ሆኖ ቀረ። የበላይ ዘለቀና የሌሎቹ አርበኞች ግፍ፤ በሰፈርከው ቁና ተሰፈር እንዲሉ፤ በላይ ዘለቀን የሰቀለው ንጉስ ራሱ ያስተማሯቸው ሰዎች እንደ እባብ ደብድበው ገድለው ሺንት ቤት ተቀበሩት። ገዳዩ መንግስቱ ሃይለ ማሪያም በሰው አገር ብቻውን ይኖራል። የዛሬዎቹ መሪዎችም ከዚህ ትምህርት መውሰድ አለባቸው። ሁሉን ኢትዮጵያዊ ባንድ እኩል አይን ማዬት ያስፈልጋል። ጉልብተኞችንና ወገን ያላቸውን ፈትተው፤ ተከራካሪ ወገን የሌላቸውን የሃባዎችን አስረዋቸው ዝም አሉ። ነውር ነው። እንዲህ አይደረግም። እስቲ ምን አደረጉ? እንደ ወያኔዎች ባመኑበት አላማ ተሰልፈው ነበር እንጂ።

አይ አያልነሽ፤ ስንቱን ዘርዝሬ ልጣፍልሽ። ሆድ ይቻለው ብሎ ዝም ማለት ይሻላል። ብቻ አይዞሽ። ይኸው እኛም ሰው ከደረሰው ደርሰን ሁሉን ነገር ከአየነው በኋላ አሁን ዱሩ ጫካው ተራራውና ወንዙ ትዝ ይለናል። ጦቢያ አንድ ነገር ብትሆን፤ እንደ አፈኛው ዳያስፖራ (ቮካል ዳያስፖራ ይሉታል) ስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ገብተን አንደነፋም ወይንም አፈ-ቀላጤ ፍልጋ አንሄድም። ከጦቢያ ህዝብ ጋር መጥተን እንሰለፋለን። በቃ ነገር ተከተተ። እልሻለሁኝ።

ጌታቸው መኳንንት
ተጣፊ
ታህሳስ 2000
በኦታዋ ካናዳ